# ስደተኛ ሴቶች



## በዲጂታል ማኅልበት እና የግንኙነት ፕሮጀክት

## ክፍል 2 - አገልግሎቶችን ለማግኘት ኦንላይ መሆን

British Red Cross

Home Office

The power of kindness

# እንኳን ደህና መጡ!



ዛሬ የሚከተሉትን እናደርጋለን:

- UK ውስጥ ያለውን የትምህርት ስርዓት መመልከት እና ኦንላይን ተደራሽነት ለዚህ እንዴት ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል መወያየት
- UK ውስጥ ሥራን እና የኦንላይን ተደራሽነት ሚና ላይ መወያየት
- ስለመኖሪያ ቤት እና የኦንላይን ተደራሽነት ሚና ላይ መወያየት

# መሰረታዊ ህጎች

- ሚስጥራዊ ቦታ
- አስተማማኝ ቦታ
- ስልኮች ይዘጉ
- አክባሪ ይሁኑ
- የማያዳላ
- አንድ በአንድ ይናገሩ
- የማይናገሩ ከሆነ Zoom ን ድምጸ-አልባ ያድርጉት
- **አንድ ነገር እንዲደገም ከፈለጉ ይጠይቁ!**

- አለማወቅ ችግር የለውም



# የ Zoom ባህሪያት













The power of kindness

# UK ውስጥ ትምህርት

UK ውስጥ ያለው የትምህርት ስርዓት በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል:



- የመጀመሪያ ዓመታት
- የመጀመርያ ደረጃ ትምህርት
- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት

በሕጉ መሰረት UK ውስጥ ያሉ ሕፃናት ከ 5*-16 ዓመት ዕድሜ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መከታተል አለባቸው፡፡

ሁሉም የዚህ ዘመን ልጆች በመንግስት በሚተዳደር ትምህርት ቤት ነፃ ቦታ የማግኘት መብት አላቸው።

- ተጨማሪ ትምህርት
- ከፍተኛ ትምህርት

የጎልማሶች ትምህርት

ኦንላይን ትምህርት ቤት ምዝገባዎች

# እያንዳንዱ ሰው የመማር መብት አለው

ዲጂታል አስተዳደግ

ዲጂታል መዝናኛ

The power of kindness

# UK ውስጥ ቅጥር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች እና ኦንላይን ተገቢ መረጃን የት እንደሚያገኙ ያስቡ፡



- መብቶችዎን እና የሚሰጥዎትን በተመለከተ UK ውስጥ ሥራ ስለመጀመር ምን ማወቅ ይፈልጋሉ?
- ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም ከቀጣሪዎ ጋር በተፈጠረው አለመግባባት እርዳታ ከፈለጉ የት መሄድ እንዳለብዎ ያውቃሉ?
- UK ውስጥ ሁሉም ሰው ለመቀጠር አንድ ዓይነት መብት አለው?

The power of kindness

# የቅጥር ደንቦች

UK ሰራተኞችን የሚጠብቅ እና አነስተኛ ደረጃዎችን የሚያረጋግጥ የቅጥር ህጎች አሉት፡

- **ብሔራዊ አነስተኛ ደመወዝ** አሠሪዎ እንደ ዕድሜዎ የሚለያይ ዝቅተኛ ሆኖ ሊከፍልዎ የሚገባውን መጠን በዝርዝር ያሳያል
- **የሥራ ሰዓት የጊዜ ደንብ** አዋቂዎች በውል ይህንን ለማድረግ በትክክል ካልመረጡ በስተቀር በሳምንት ከ 40 ሰዓታት በላይ መሥራት እንደሌለባቸው ይደነግጋል
- የሰራተኞችን ደህንነት ለመጠበቅ የታቀዱ ብዙ **የጤና እና ደህንነት ህጎች** እና ደንቦች፡፡
- ጥበቃ በሚደረግለት ባህሪ (ዕድሜ ፣ ዘር ፣ ጾታ ፣ወሲባዊነት ፣ ሃይማኖት ፣ ጾታ ፣ የአካል ጉዳተኝነት ወዘተ) ምክንያት አሠሪዎ በተለየ ሁኔታ ሊይዝዎ እንደማይችል የሚገልጹ **የመድልዎ ሕጎች**
- **የተከፈለበት የእረፍት ጊዜ ፣ የህመም እና የወሊድ ወይም የአባትነት የእረፍት ፈቃድ ሕጎች** በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ደመወዝ የሚከፈላቸው የእረፍት ጊዜ እና መጠን የሚገልጹ ናቸው፡፡
- አሠሪዎ የጡረታ አደረጃጀት እንዲኖረው የሚያስገድዱ **የጡረታ መዋጮ ሕጎች**

The power
of kindness

# በ COVID-19 ምን ተለውጧል?



መረጃ የት ይገኛል?





The power of kindness

# UK ውስጥ መኖሪያ ቤት

## እውነት ወይም ሀሰት:

- ዩኒቨርሳል ክሬዲት ከተቀበሉ የመኖሪያ ቤት ወጪዎች ሁል ጊዜ ይሸፈናሉ።
- የምክር ቤት መኖሪያ ቤት/ማህበራዊ መኖሪያ ቤት (በአከባቢው ባለስልጣን የተያዘ መኖሪያ ቤት) መብት ነው ስለሆነም እርስዎ ከጠየቁ ሁልጊዜ ይህንን እገዛ ያገኛሉ፡፡
- ቤት አልባ ከሆኑ ምክር ቤቱ ሊረዳ ይችላል፡፡
- ለምክር ቤት መኖሪያ ቤት ማመልከት 'በጣም ከአስፈላጊነት' አንጻር ይወሰናል።
- አንዴ ፍላጎቴን ለምክር ቤቱ ከነገርኩ በኋላ ሁሉንም ነገር አስተካክለው ቋሚ የምኖርበት ቦታ ያገኙልኛል፡፡



The power of kindness

ዛህራ እና ልጆቿ በስደተኛ የቤተሰብ ውህደት ቪዛ ከኢጋሯ ጋር ለመኖር UK መጡ፡፡ ዛህራ ፣ በዚህ የቪዛ ምድብ ውስጥ ከመኖሪያ ቤት ጋር የተያያዙትን ጨምሮ የህዝብ ገንዘብ የማግኘት መብት እንዳላት ታውቃለች፡፡ ኢጋሯ በአሁኑ ጊዜ በጋራ ቤት ውስጥ ስለሚኖር ቤተሰቡ በአንድ ክፍል ውስጥ መተኛት አለባቸው ስለዚህ አዲስ ቤት መፈለግ አለባቸው ፡፡ ተጨናንቀዋል፡፡ እሷ እና ቤተሰቧ የአከባቢውን ባለስልጣን ጎብኝተው በአማራጮቻቸው ላይ ምክር እንዲያገኙ እና አዲስ ቤት ለመፈለግ እንዲረዱ ጠይቀዋል፡፡

ዛህራ UK ውስጥ ስለኖረችበት ቦታ ሁሉ መረጃ እንዴት እንደምትሰጥ ተጠይቃለች፡፡ በቅርቡ እንደመጣች እና ከዚህ በፊት UK ውስጥ ሌላ ቦታ አለመኖሯን ገልጻለች፡፡ ምክር ቤቱ ቤተሰ ቧን በተጠባባቂነት ዝርዝር ላይ በማስቀመጥ ቤተሰቡ ለምክር ቤት ይዞታ ለመወዳደር መዝግበዋል፡፡ ከመጠን በላይ የተጨናነቁ መሆናቸውን አምነው በሆቴል ውስጥ 5 ማይሎች ርቆ ወደሚገኘው ድንገተኛ መጠለያ እንዲወስዷቸው እና ለማህበራዊ መኖሪያ ቤቶች ለመጫረት እንዲያስመዘግቧቸው እንዲሁም የግል ኪራይ እንዲፈልጉ ይመክራሉ፡፡

The power of kindness

# የቤተሰብ ውህደት እና የስደተኛ ቪዛዎች ባለቤቶች

- **የቅድመ-በረራ እና የድህረ-በረራ አጋሮች** አማራጮቻቸውን ለማጣራት የሕግ ምክር መፈለግ አለባቸው፡፡
- **የስደተኛ ቪዛ ሁኔታ** ብዙ አማራጮች አለው

- በቤትዎ ውስጥ ደህንነትዎ እንደተጠበቀ መኖር
- በሴቶች መጠለያ ውስጥ ቦታ ማግኘት
- ከአከባቢው ምክር ቤት ድጋፍ መፈለግ፡፡

## የቤት እጦት ማመልከቻ

- **አሁን ቤት አልባ ነዎት**
- **የስደት ሁኔታዎችን ያሟላሉ**
- እርስዎ ተቀዳሚ ፍላጎት አለዎ፡ በጾታዎ ምክንያትን ጨምሮ በቤት ውስጥ ጥቃት የመድረስ አደጋ ተጋርጦበታል
- እርስዎ ሆን ብለው ቤት አልባ አይደሉም
- ~~የአካባቢ ግንኙነት አለዎት፡~~-ለቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባዎች አይደለም

The power of kindness

sheffieldpropertyshop.org.uk

# Welcome to the Property Shop

Welcome to the Property Shop, Sheffield City Council's new website for allocating Council and partner Housing Association properties for rent in Sheffield.

We aim to give you more choice in deciding where you want to live. Properties that are available for rent will be advertised each week.

To begin using the site, please Login or Register. Alternatively, further information regarding the application process can be found here.

**Read more ▸**



## Advertising dates

**5**
days left
to bid

**Current cycle**
4 Mar, until 9 Mar

**Next cycle**
Starts 11 Mar, until 16 Mar

## Latest news

**Providing ID and a Reference**

Early on in the Covid-19 pandemic, the Council announced that we would not require identification and a landlord reference to join the Housing Register due to the closure of our in-person access points. The Council advised that these would be requested at a later date.
We are now...
*Published: Tuesday 16 February 2021*

**View all news ▸**

## Log In to Your Account

Click here to log in to your account and create a new rehousing application, update an existing application or complete your annual review.

**Log In Here**

ለምክር ቤት መኖሪያ ቤቶች ምዝገባና ጨረታ

The power of kindness

# የግል ኪራይ







- ኪራዩ ስንት ነው?
- የፍጆታ ክፍያዎችስ?
- የምክር ቤት ግብር ስንት ነው?
- ቤቱ እቃ ተሟልቷል?
- የግል አከራይ ነው ወይስ በአከራይ ወኪሎች በኩል?
- ተቀማጭ ገንዘቤ ይጠበቃል?
- ውሉ ለምን ያህል ጊዜ ነው?

The power of kindness

# የኦንላይን ሂሳብ/መለያ መፍጠር

- የተጠቃሚ ስም
- ኢሜል አድራሻ
- የይለፍ ቃል
- የደህንነት ጥያቄዎች
- የአድራሻ ዝርዝሮች
- ለዚያ ልዩ አገልግሎት ሌላ ምን ጠቃሚ ነገር አለ?

The power of kindness

# ድህረ-ገጾችን መተርጎም







- በቀኝ መጫን
- ሌላ ቋንቋ ይምረጡ (እነዚህ በእንግሊዝኛ ፊደል ተዘርዝረዋል)
- የትርጉም (Translate) ቁልፍ ይጫኑ።
- የራስ-ሰር (አውቶማቲክ) ትርጉም ሰው እንደሰራው ትርጉሞች ትክክለኛ ወይም ግልጽ ላይሆን እንደሚችል ልብ ማለት ተገቢ ነው፡፡

The power of kindness

# ማጠቃለያ

ዛሬ የሚከተሉትን አከናውነናል:

- UK ውስጥ ስለ ትምህርት ፣ ሥራ እና መኖሪያ ቤት አንዳንድ ቁልፍ መረጃዎችን ተወያይተናል፣
- እነዚህን ለማግኘት ኢንተርኔት እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል አንዳንድ ምሳሌዎችን ተወያይተናል፣
- አገልግሎቶችን ለማግኘት የኢንላይን ሂሳብ/መለያ ለመፍጠር ጠቃሚ ምክሮችን ተመልክተናል
- የራስ-ሰር (አውቶማቲክ) ትርጉም በድረ-ገጾች ላይ እንዴት እንደሚጠቀሙ ተመልክተናል፡፡



# ቁልፍ ቃላት

**ራስ-ሰር (አውቶማቲክ) -** ከሰው ይልቅ በራስ-ሰር መሳሪያዎች የሚሰራ፡፡

**የግዴታ ትምህርት -** ልጆች በመደበኛ ትምህርት ውስጥ እንዲሆኑ በሕጋዊ መንገድ የሚፈለግበት ጊዜ፡፡

**የምክር ቤት መኖሪያ ቤት -** ጥራትንና አቅምን የመጠበቅ ሃላፊነት ያለው በአከባቢው ባለስልጣን የተያዘ መኖሪያ ቤት፡፡

**የቅጥር ሕግ -** የሠራተኛ እና አሠሪዎችን መብቶች የሚቆጣጠሩ የሕጎች ስብስብ።

**የኦንላይን ሂሳብ/መለያ -** አንድ የተወሰነ አገልግሎት ለማግኘት የግል መረጃ ዝርዝሮች ምዝገባ።

**የግል ኪራይ -** እንደ ንብረት ያሉ በግል ባለቤትነት የተያዘ ነገር ለመጠቀም መክፈል።

**የመንግስት ገንዘብ -** ዝቅተኛ ገቢን መሠረት በማድረግ የሚሰጥ የበጎ አድራጎት ድጋፍ ፣ ጥቅማጥቅሞች እና የቤት ድጋፍ።

**ትርጉም -** ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላው ማስተላለፍ፡፡

The power of kindness